# የBox ፈጣን የማጣቀሻ መምሪያ
# የውጭ ተጠቃሚዎች

## አላማ


Box ለ የስቴቱ የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ [Office of the State Superintendent of Education (OSSE)] አዲስ አስተማማኝ የዳታ ማስተላለፊያ ሲስተም ነው። ይህ ሲስተም በOSSE እና የውጭ ተጠቃሚዎች መካከል አስተማማኝ የዳታ መጋራትን የሚረዳ መሳሪያ ነው።

## ማግኘት

Box OSSE በመደበኛ ሁኔታ የሚያጋራቸው በቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶች እና ግላዊ ሚስጥር (Family Educational Rights and Privacy Act, FERPA) የሚጠበቁ ዳታን የሚይዝ አቃፊዎች አሉት። ይህ የኮሎምቢያ ግዛት የአካባቢው የትምህርት ኤጀንዲዎች (local education agencies, LEAs) (የኮሎምቢያ ግዛት የህዝብ ትምህርት ቤቶች፣ ወይም DCPS፣ እና የህዝብ ቻርተር LEAs ሁለቱም)፣ የኮሎምቢያ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ቦርድ ( Public Charter School Board, PCSB)፣ እና ማህበረሰብ መሰረት ያደረጉ ድርጅቶችን ያካትታል። OSSE ለአቃፊዎች እና ማንኛውም ንኡስአቃፊዎች ፕሮጀክትን መሰረት ባደረገ መልኩ ፍቃዶች ይሰጣል።

እንዲገቡ የተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች ከOSSE ወደ Box የሚያስገባ የግንኙነት መስመርን ጨምሮ ኢሜይል ይደርሳቸዋል። የውጭ ተጠቃሚው የBox አካውንት ከሌለው፣ ተጠቃሚው አንድ እንዲፈጥር ይገፋፋል። ሁሉም ቦታዎች እንደተሞሉ፣ **Submit** (አስገባ) የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ።

ሁሉም ተጠቃሚዎች ዝቅተኛ የሆነውን ቢያንስ ስምንት አይነተ-ፊደል፣ የቁጥሮች፣ ትልቁ ፊደሎች፣ ወይም ልዩ አይነተፊደሎች ድብልቅ (ማለትም፣ $#@&!) መስፈርትን ያሟላ የይለፍ ቃሎች ሊኖራቸው ይገባል።


Box Collaborator Sign Up

'DC Government' Has Invited You to Collaborate on 'From OSSE'

Your Information

Full Name

Test user

Email Address

Testuser@LEA.edu

Password

•••••••••••••• Good

Phone Number


202-000-0000

Submit

By registering you agree to Box's Terms of Service and Privacy Policy.


*ስእል 1፣ ይመዝገቡ*

ቀጥሎ፣ የማሳያ መስኮቱ ይመጣል። **Skip this and go straight to Box** (ይህን እለፍ እና በቀጥታ ወደ Box ሂድ) የሚለውን ይምረጡ።





*ስእል 1፣ የእንኳን ደህና መጡ መልእክት*

ግብዣዎችን ያዘለ የመልእክቶች ማቀፊያ በዋናው ዳሽቦርድ ላይ ይመጣል። ተጠቃሚው በመጠባበቅ ላይ ያሉትን ግብዣዎች ለመመልከት **Messages** (መልእክቶች) የሚለውን ይጫናል።





*ስእል 3፣ ዋና ዳሽቦርድ*

የአገልግሎት የስምምነት ቃላትን ይመርምሩ እና **Agree and Accept** (ተስማማ እና ተቀበል) የሚለውን ቁልፎች ይጫኑ። ውጫዊ ተጠቃሚው የአገልግሎት የስምምነት ቃሎችን አንድ ጊዜ ከተቀበለ በኋላ፣ ከOSSE ተከታይ ግብዣዎች አውቶማቲክ በሆነ መልኩ ተቀባይነት ያገኛሉ።





*ስእል 4፣ በመጠባበቅ ላይ ያሉ ግብዣዎች*

ብቅ ባይ የማሳያ መስኮት ይመጣል። ወደ “ወደ OSSE” አቃፊው ለመሄድ **Yes** (አዎ) ይጫኑ።




*ስእል 5፣ ትብብሩ ተቀባይነት አግኝቷል*

ዋናው ዳሽቦርድ አሁን ሁሉንም የፕሮግራም አቃፊዎች ያሳያል።





*ስእል 6፣ ዋናው ዳሽቦርድ ከፕሮግራም አቃፊዎች ጋር*

## ወደ OSSE

በ"ወደ OSSE" ማቀፊያ ውስጥ፣ ተጠቃሚው የአርታኢ ፍቃድ አለው። እንደ አርታኢ፣ ተጠቃሚው ፋይሎችን ሊጭን እና ሊሰርዝ ይችላል(ለተጨማሪ መመሪያ ይመልከቱ**Appendix A: User Permissions**)። ወደ OSSE ፋይሎችን ለመላክ፣ ተጠቃሚው ፋይሎችን ተገቢ ወደ ሆነው "ወደ OSSE" የፕሮግራም ማቀፊያ ይጭናል።


**ማስታወሻ፣** ፋይሎች ከ60 ቀናት በኋላ ጊዜያቸው የሚያልፍ እና በራሳቸው እንዲሰረዙ ሆነው ይዘጋጃሉ።




*ስእል 2፣ "To OSSE" ("ወደ OSSE") ማቀፊያ፣*

ወደ ማቀፊያ ዳታ ለመጫን፣


1. ተገቢ የሆነውን አቃፊ መጫን።
2. **Upload** (ጫን) የሚለውን ቁልፍ መጫን።
3. ፋይሎች ወይም አቃፊዎች የሚለውን መምረጥ።
4. በኮምፒውተርዎ ላይ ዳታውን መፈለግ።
5. ለመጫን **Open** (ክፈት) የሚለውን መጫን።




*ስእል 3፣ "To OSSE" ("ወደ OSSE") አቃፊን መጫን*

ፋይል ወይም አቃፊን ለማስወገድ፣ ፋይሉ ላይ ወይም አቃፊው ላይ ይጫኑ።

1. **More Options** (የበለጠ አማራጮች) ምልክት ላይ መጫን።
2. **More Actions** (የበለጠ ተግባሮች) ላይ መጫን።
3. **Trash** (መጣያ) ላይ ይጫኑ።





*ስእል 4፣ ፋይልን ማስወገድ*

ብቅ ባይ የማሳያ መስኮት ይመጣል፣ ስረዛውን ለማረጋገጥ **Okay** (እሺ) ይጫኑ።

## From OSSE (ከ OSSE)

OSSE ፋይሎችን ለማጋራት From OSSE (“ከ OSSE”) ማቀፊያን ይጠቀማል። OSSE አቃፊዎችን ያጋራቸው ተጠቃሚዎች የተመልካች ፍቃድ ይኖራቸዋል። የተመልካች ፍቃድ ያላቸው ተጠቃሚዎች በ From OSSE (“ከ OSSE”) ማቀፊያ ውስጥ ያሉትን ፋይሎች ወይም አቃፊዎች ሊሰርዙ አይችሉም።





*ስእል 5፡ From OSSE (“ከ OSSE”) ማቀፊያ*


## ፋይሎችን መፍጠር

ፋይሎችን በ All Files (“ሁሉም ፋይሎች”) እና To OSSE (“ወደ OSSE”) ማቀፊያዎች ውስጥ መፍጠር ይችላሉ። በ All Files (“ሁሉም ፋይሎች”) ውስጥ ፋይል ለመፍጠር፣

1. **New** (አዲስ) ላይ ይጫኑ።
2. ወደታች በሚወርደው ዝርዝር፣የሚፈጠረውን ንጥል አይነት ይምረጡ።




3. ፋይሉ ወይም አቃፊው **All Files** (ሁሉም ፋይሎች) ገጽ ላይ ይመጣል።





*ስእል 6፡ ፋይል ፍጠር*




*ፋይል ፍጠር*

**ማስታወሻ፣** ፋይል ወይም አቃፊ ወደ To OSSE (“ወደ OSSE”) ወይም From OSSE ( “ከ OSSE”) አቃፊዎች ሊዛወር ይችላል። ፋይልን ወይም አቃፊን ለማዛወር፣ ንጥሉ ላይ ይጫኑ እና ወደ OSSE To OSSE (“ወደ OSSE”) ወይም From Osse (“ከ OSSE”) አቃፊዎች ይጎትቱት።




*ስዕል 7፣ ፋይልን ማዛወር*


ብቅ ባይ የማሳያ መስኮት ይመጣና፣ ንጥሎችን በOSSE ወደተፈጠሩ አቃፊዎች ማዛወር የፋይሉን ባለቤትነት ወደ OSSE እንደሚያዛውር ያሳውቀዋል።




*ስዕል 8፣ የባለቤትነት ለውጥ ማሳወቂያ*

## የይለፍ ቃል እንደገና ማዘጋጀት

የይለፍ ቃል እንደገና ለማዘጋጀት፣ **Reset Password** (የይለፍ ቃል እንደገና አዘጋጅ) የሚውን በመግቢያው ገጽ ላይ ይጫኑ። የተሰጡትን መመሪያዎች ይከተሉ እና **Reset Password** (የይለፍ ቃል እንደገና አዘጋጅ) የሚለውን ይምረጡ።




*ስእል 9፣ የይለፍ ቃል ማዘጋጀት*

## አባሪ A፣ የተጠቃሚ ፍቃዶች

የBox ከሁለት አንድ ፍቃዶች አላቸው፣ አርታኢ ወይም ተመልካች። በ To OSSE (“ወደ OSSE”) አቃፊ ላይ ያሉ ተጠቃሚዎች የአርታኢ ፍቃድ ይኖራቸዋል። በ From OSSE (“ከ OSSE”) አቃፊ ላይ ያሉ ተጠቃሚዎች የተመልካች ፍቃድ ይኖራቸዋል።

| ፍቃዶች | | |
|---|---|---|
| | **አርታኢ** | **ተመልካች** |
| አውርድ | አዎ | አዎ |
| አስተያየቶችን ተመልከት / ጨምር* | አዎ | አዎ |
| ፋይሎች/አቃፊዎች አጥፋ | አዎ | |
| ስራዎችን ተመልከት/ፍጠር | አዎ | አዎ |
| መለያዎችን ጨምር/አሻሽል | አዎ | |
| መለያዎችን ተመልከት | አዎ | አዎ |
| Metadata ተመልከት | አዎ | አዎ |
| Metadata አሻሽል | አዎ | |
| ሰዎችን ጋብዝ | አዎ | |
| የአቃፊ ስም አሻሽል | አዎ | |
| ንኡስ አቃፊዎችን ፍጠር | አዎ | |
| የአቃፊ አቀማመጥ አሻሽል | | |
| ቅድመእይታ | አዎ | አዎ |
| ፋይል መቆለፍ/መክፈት | አዎ | |
| መመልከት-ብቻ የግኙነት መስመር መላክ | አዎ | |
| ጫን | አዎ | |
| በአቃፊ ውስጥ የንጥል ዝርዝር መመልከት | አዎ | አዎ |
| አቃፊ አቀናብር | አዎ | |
| የመግቢያ ፍቃዶችን አዘጋጅ | አዎ | |
| ግብዣዎችን ገድብ | | |
| የመግቢያ ስታቲስቲክሱን ተመልከት | አዎ | |
| አዛውር | አዎ | |
| ኮፒ | አዎ | ** |

*አስተያየቶች ሊሰረዙ የሚችሉት በአቃፊው ባለቤት ወይም አስተያየቱን በፈጠረው ሰው ብቻ ነው።

**ተመልካች በBox ውስጥ ፋይልን ኮፒ ማድረግ አይችልም፣ ነገር ግን ተመልካቾች ፋይሉን ማውረድ እና ሌላ የትኛውም ቦታ መጫን እንደሚችሉ፣ ወይም ፋይሉን መክፈት እና ይዘቶቹን ወደሌላ ፋይል ኮፒ በማድረግ መለጠፍ እንደሚችሉ ግን ማወቅ ያስፈልጋል።